በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# በጥቅምት ወር 1987 በተካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት የሥራ አፈጻጸምን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ ሪፖርት

19 ሕ ቤ ቆ ኮ 87

አዲስ አበባ
ጥር 20 ቀን 1989

**በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር**
**የማዕከላዊ እስታትስቲክስ ባለሥልጣን**

# በጥቅምት ወር 1987 በተካሄደዉ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት የሥራ አፈፃፀምን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ ሪፖርት

**አዲስ አበባ**
**ጥር 20 ቀን 1989**

## አርዕስት

ገጽ

1. መግቢያ 1

2. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም፣ አስፈላጊነትና ዓላማዎች 2

2.1. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም 2
2.2. የሕዝብና ቤት ቆጠራ አስፈላጊነት 3
2.3. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዓላማዎች 4

3. የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ 5

3.1 የ1976 የሕዝብና ቤት ቆጠራ 5
3.2 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ 5

4. የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማካሄድ የተከናወኑ ዓበይት ተግባራት 6

4.1 የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተ 7
4.2 ዋናውን ቆጠራ ማካሄድ 18
4.3 የድኅረ ቆጠራ ሥራዎች 22

5. የሪፖርት ዝግጅት ሕትመትና ሥርጭት 27

5.1. በአፋርና በሶማሌ ብሄራዊ ክልሎች ድጋሚ ቆጠራ ለማካሄድ የተከናወኑ የዝግጅት ተግባራት 29

6. በ1989 የሚከናወኑ ቀጣይ ተግባራት 30

7. ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈፀሚያ በሥራ ላይ የዋለ በጀት 30

7.1. በመንግሥት ከተመደበዉ በጀት በሥራ ላይ የዋለ መጠን 31
7.2. ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የተገኘ ገንዘብን በሚመለከት 31

8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 32
9. ማጠቃለያ 34

በጥቅምት ወር 1987 በተካሄደዉ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት

የሥራ አፈፃፀምን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

የቀረበ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታን የሚያንጸባርቁ መረጃዎች ማለትም የሕዝብ ብዛት፣ የልደት፣ የሞት፣ የፍልሰት፣ የቤቶች፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የሥራ ሁኔታ፣ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የትራንስፖርት፣ የንግድ ... ወዘተ. የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ለሚደረገዉ ማህበራዊና-ኢኮኖሚያዊ ልማት ዕቅድ ማዘጋጃ ያገለግላሉ። በተጨማሪም መረጃዎች የማህበራዊና-ኢኮኖሚያዊ ልማት ዕቅድ ያስገኘዉን ዉጤት ለመገምገምና ለመከታተል፣ ለቁጥጥር፣ ለጥናትና ለአስተዳደር ይጠቅማሉ። እነዚህን የማህበራዊና የኢኮኖሚ መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚቻለዉ በተለያዩ ዘዴዎች ሲሆን ከዘዴዎቹ ዋና ዋናዎቹ:- ጠቅላላ ቆጠራ ለማካሄድ፣ ናሙና ጥናት በማካሄድ፣ የማያቋርጥ ምዝገባ በማካሄድ፣ ከአስተዳደር መዛግብት መረጃዎችን በማጠናቀር ናቸዉ።

የሕዝብና የቤትን የሚመለከቱ መረጃዎችም ከላይ ከተጠቀሱት የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ሁሉ መሠረት ሊገኙ የሚችሉ ሲሆን ይህ ጽሁፍ የሚያተኩረዉ የሕዝብና ቤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በጠቅላላ ሕዝብና ቤት ቆጠራ በማካሄድ በመሰብሰብ ላይ ነዉ።

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ከተጣለበት የሥራ ድርሻ አንዱ የሀገሪቱን የሕዝብ ብዛትና ስርጭት፣ የሕዝቡን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዴሞግራፊያዊ ባህሪያት በማጥናት ልዩ ልዩ አመልካቾችን ማጠናቀር፣ ሕዝብ ነክ ሁኔታዎች ከማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር ያላቸዉን ተዛምዶ በመመርመር ለዕቅድ አዘጋጆች፣ ለፖሊሲ አዉጭዎች፣ ለአስተዳዳሪዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለምርጫ አስፈጻሚዎችና በአጠቃላይ ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት ነዉ።

በመሆኑም ለዚህ ዓላማ ተፈጻሚነት በአገር አቀፍ ደረጃ ለሁለተኛ ጊዜ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በአብዛኛዉ የአገሪቱ ክልሎች ከጥቅምት 1-10 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ ባሉት ቀናት ተካሂዷል። ቆጠራዉን ለማካሄድ በርካታ ቁሳቁስ፣ ብዛት ያለዉ የሰዉ ኃይል፣ ሰፊ

የሎጆስቲክ ድጋፍና ከፍተኛ ገንዘብ በማንቀሳቀስ ቆጠራዉን በተሣካ ሁኔታ ለማካሄድ ተችሏል።

በዚህ አጋጣሚ ስለፐሮጀክቱ የ1988 የሥራ ክንዋኔ ሪፖርት ብቻ ከማቅረብ ፋንታ ምክር ቤቱ ስለተካሄደዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የበለጠ ግንዛቤ እንዲያገኝ አጠቃላይ የሥራ ሂደቱን ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበናል።

በመሆኑም በዛሬዉ ዕለት የሚቀርበዉ ሪፖርት ይዘት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም፣ አስፈላጊነትና ዓላማ፣ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ፣ ሁለተኛዉን አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ የተከናወኑት ልዩ ልዩ የዝግጅት ሥራዎች፣ የዋናዉ ቆጠራ አጠቃላይ እንቅስቃሴ በቆጠራዉ የተደረገ ወጪ፣ የሪፖርት ዝግጅትና ስርጭትን በቆጠራዉ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች አጠቃላይ ሪፖርት እንደሚከተለዉ አቀርባለሁ።

## 2. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም፣ አስፈላጊነትና ዓላማዎች

### 2.1. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም፣

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ባጭሩ ሲገለጽ በተወሰነ ወቅትና በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በአገር ዉስጥ በተወሰነ የአስተዳደር ክልል ስላለዉ ሕዝብና ስለሚገኙት ቤቶች ብዛት፣ ስለ ሕዝቡ ዲሞግራፊያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት እንዲሁም ስለቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ የማጠናቀርና ብሎም የመረጃዉን ጥራት አስተማማኝነቱንና ትክክለኛነቱን በመገምገም የተገኘዉን ወጤት ለተጠቃሚዎች የማቅረብ ተግባራትን ያጠቃልላል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዉጤት ከአነስተኛ የአስተዳደር አካል ማለትም በገጠርና በከተማ ከቀበሌዎች ጀምሮ እስከ ብሄራዊ ክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ መረጃዎችን ያስገኛል።

## 2.2. የሕዝብና ቤት ቆጠራ አስፈላጊነት፣

በአብዛኞቹ አገሮች የሕዝብና ቤት ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ የሚካሄድ ፕሮጀክት ሲሆን ከቆጠራዉ የሚገኘዉ መረጃም የሀገሮችን ወቅታዊና አስተማማኝ የሆነ የማሕበራዊና የኢኮኖሚ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ዕቅዶችን ለመንደፍ፣ ተግባራዊነታቸዉንም ለመከታተልና ለመገምገም አስፈላጊ ናቸዉ። በተጨማሪም በአገር አቀፍ ደረጃና በተወሰነ የአስተዳደር ክልል ዉስጥ ለሚደረጉት ሕዝባዊ ምርጫዎችን አፈጻጸም በተመለከተ የመራጮችና የተመራጮች ብዛት፣ እንዲሁም የምርጫ ክልሎችን ለይቶ ለማወቅ ወሳኝ ሚና አለዉ።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነዉ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በግንቦት 1976 ዓ.ም መካሄዱ ይታወሳል። ከዚህ ቆጠራ በኋላ የተከሰቱትን ለዉጦች ለመገምገም፣ አዳዲስ መረጃዎችንም በብቃትና በጥራት ለማስገኘት እንዲሁም የሕዝቡን የወደፊት የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የዲሞግራፊያዊ ባህሪያትን አስተማማኝና ወቅታዊ ለማድረግና ከዲሞግራፊያዊ መረጃዎችም ላይ በመነሣት የሕዝቡን ብዛት ለመተንበይ እንዲቻል ነዉ። በተጨማሪም በ1976 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ወቅት በተለያዩ ምክንያት ያልተሸፈኑትን የሀገሪቱን ክፍሎችና ሕዝቦች ሙሉ በሙሉ ለመሸፈን እንዲቻል ሁለተኛዉ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በ1987 ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የ1976 ቆጠራ ከተካሄደ በኋላ በ1977 የነበረዉ ረሀብ፣ በአርሶ አደሩ ፍላጎት ላይ ያልተመሠረተ የመንደር ምሥረታና፣ የሠፈራ ፕሮግራም፣ ከግንቦት 1983 በፊት የነበረዉ ጦርነት፣ ከግንቦት 1983 በኋላ የተከሰተዉ የፖሊሲ ለዉጥ ግንባር ቀደሞቹ ናቸዉ። የእነዚህ ክንዉኖች በሕዝቡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲሞግራፊያዊ ሁኔታዎች እንደዚሁም በሕዝቡ ዲሞግራፊያዊ ስርጭት ላይ የሚያስከትሉት ተፅዕኖ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

## 2.3. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዓላማዎች

በ1976 በተካሄደዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተሰበሰበዉ መረጃ ወቅታዊዉን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ያሳያል ብሎ መገመት ያስቸግራል። ስለሆነም የሀገሪቱን ሕዝብና ቤቶች በሚመለከት ለሚነሱት መሰረታዊ የመረጃዎች ጥያቄ የተሟላ፣ አስተማማኝና ወቅታዊ መልስ ለመስጠት እንዲቻል በአገር አቀፍ ደረጃ ለሁለተኛ ጊዜ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መካሄድ አስፈላጊ ነበር። በዚህም መሠረት በ1987 ለተካሄደዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ።

### 2.3.1. ስለሕዝብ ብዛት መረጃዎች ማግኘትን በተመለከተ፣

የቆጠራዉ ዉጤት ወቅታዊና አስተማማኝ የሆኑ የሕዝብ ብዛትን በዕድሜና በፆታ የሚያመለክቱ መረጃዎችን በገጠርና በከተማ፣ በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ለማግኘት፣

### 2.3.2. ስለ ሕዝቡ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕሪያትን በተመለከተ፣

የሕዝቡን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ባህሪያት ማለትም እንደ ብሄረሰብ፣ ቋንቋ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ዓይነት ...ወዘተ መረጃዎችን በገጠርና በከተማ፣ በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ ደረጃ ለማግኘት፣

### 2.3.3. ስለ ሕዝቡ የዲሞግራፊ ባህሪያትን መረጃ በተመለከተ፣

የሕዝቡን የየዓመቱ ዕድገት መጠን ለማስላትና የሕዝቡን ብዛት በሚቀጥሉት አምስት፣ አሥር ወይም ከዛ በላይ ላሉት ዓመታት ትንበያ ለማዘጋጀት የሚረዱ እንደ ልደት፣ ሞትና ፍልሰት መጠን የሚያሳዩ መረጃዎችን በገጠርና በከተማ፣ በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ለማግኘት፣

### 2.3.4. ስለ ቤቶች ሁኔታን በተመለከተ፣

የቆጠራዉ ዉጤት በአገሪቱ ዉስጥ ወቅታዊና አስተማማኝ የሆኑ የቤቶችን ብዛትና፣ ሁኔታ (ዉሀ፣ መብራት፣ መፀዳጃ...ወዘተ) የሚያመለክቱ መረጃዎች በገጠር፣ በከተማ፣ በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞንና፣ በወረዳ፣ ደረጃ ለማገኘት፣

### 2.3.5. ስለሕዝባዊ ምርጫ ማስፈጸሚያ የሚረዱ መረጃዎችን በተመለከተ፣

ለሕዝባዊ ምርጫ ማስፈጸሚያ የሚረዱትን ማለትም የምርጫ ክልሎችን ለመወሰንና ለመለየት የሚጠቅመዉን የሕዝብ ብዛት በዝቅተኛ የአስተዳደር ክፍሎች እንዲሁም የመራጮችንና የተመራጮችን ብዛት የሚያመለክቱና የመሳሰሉትን መረጃዎች ለማገኘት ናቸዉ፣

## 3. የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ

### 3.1 የ1976 የሕዝብና ቤት ቆጠራ

በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደው በ1976 ዓ.ም ሲሆን ከዚህ በፊት ግን በአዲስ አበባ ከተማ በ1953፣ በ1960 እና በ1970 ዓ.ም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተካሂዷል። ተመሳሳይ ቆጠራዎችም በሌሎቹ የሀገሪቱ ጥቂት ከተሞች ተካሂደዋል። በአርሲም በ1964 ዓ.ም. የሕዝብና የከብቶች ቆጠራ ተካሂዷል።

### 3.2 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ

የ1987 ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባራዊ ለማድረግ የሕዝብና ቤት ቆጠራ አዋጅ ቁጥር 32/1985 ወጥቷል። በዚህ አዋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃና ከዚያም በተዋረድ እስከ አነስተኛው የአስተዳደር ክፍል የሕዝብና ቤት ቆጠራን ሥራ የሚያስፈጽሙ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽኖችና ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል።

በመሠረቱ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባር በሚካሄድበት ሀገር ያለውን ሕዝብና ቤት ሙሉ በሙሉ መሸፈን ስላለበት ለሁለተኛ ጊዜ በተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ያለውን ሕዝብና ቤት ሁሉ ጭምር እንዲሸፍን ተደርጓል።

## 4. የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማካሄድ የተከናወኑ ዓበይት ተግባራት፥

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ከላይ በተጠቀሰዉ አዋጅ መሠረት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ሴክሬታሪያት ሆኖ እንደሚያገለግል ተጠቅሷል። በመሆኑም የ1987 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት በተሳካ ሁኔታ ለማስፈፀም እንዲቻል ያለዉን የሰዉ ኃይል /ባለሙያና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች/ የሎጂስቲክስና የገንዘብ አቅምን በማቀናጀት፥ በዕቅድ ላይ በመመርኮዝና የአፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት አካሂዷል። የቆጠራዉን ሂደት፥ በሶስት ዓበይት ደረጃዎች (Phases) በመከፈል ሥራዉን በፕሮግራም እንዲከናወኑ አድርጎዋል። እነሱም፥

- የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ሥራዎች ማካሄድ፥
- ዋናዉን ቆጠራ ማካሄድ፥ እና
- የድህረ ቆጠራ ሥራዎችን ማካሄድ ናቸዉ።

በመሆኑም ቆጠራዉን ከላይ በተጠቀሱት ደረጃዎች ለማስፈፀም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሚከተሉትን ኮሚቴዎች አቋቁሞ ነበር። እነዚህም፥

ሀ) የቆጠራ ካርታ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴ፥

ለ) የቆጠራ መጠይቆች መመሪያዎች አዘጋጅ ወዘተ.. ቴክኒክ ኮሚቴ፥

ሐ) የሎጅስቲክስ አደራጅ ኮሚቴ፥

መ) የሕዝብና ቤት ቆጠራ ድርጅታዊ መዋቅር አዘጋጅ ኮሚቴ፥

ሠ) የትምህርትና ቅስቀሣ ቴክኒክ ኮሚቴ፥

ረ) በከብት እርቢ አካባቢዎች የቆጠራ ዘዴ አጥኚ ኮሚቴ ናቸዉ።

ሁለተኛውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ አካሂዶ ዳር ለማድረስ ከላይ በተዘረዘሩት ኮሚቴዎች አማካኝነት የሚከተሉት ዓበይት ተግባራት ተከናውነዋል። እነርሱም:-

## 4.1. የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተ፣

የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ሥራዎች ዋናዉ ቆጠራ ከመካሄዱ በፊት መከናወን ያለባቸዉ ተግባራት ሲሆኑ ከእነዚህም የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ።

### 4.1.1. የቆጠራ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራን በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ በቅደም ተከተል መከናወን የሚገባቸዉ ሥራዎች፣ በቆጠራዉ የሚሰማራዉ የሰዉ ኃይል ብዛትና ዓይነት፣ ለቆጠራዉ የሚፈለገዉ የሎጂስቲክስ ድጋፍ፣ ቆጠራዉን ማስፈጸም የሚያስችል በጀት እንደዚሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ጭምር ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ዕቅድን የሚገልጽ ዶኩመንት ተዘጋጅቷል።

### 4.1.2. የሕዝብና ቤት ቆጠራ አዋጅ ማዉጣት፣

በ1987 የተካሄደዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በአዋጅ ቁጥር 32/1985 ተደግፎ በይፋ ለሕዝቡ ተገልጿል። የሕዝብና ቤት ቆጠራ አዋጅ ያስፈለገበት ምክንያት ጠቅላላ ህብረተሰቡ የቆጠራዉን ዓላማና ጥቅሞች በመረዳት ለቆጠራዉ ተግባር የሚሰጠዉ ትብብር ከፍተኛ እንዲሆንና መረጃ በመስጠት ረገድ ተባባሪ እንዲሆን እንዲሁም ቆጠራዉ በሕግ የተደገፈ መሆኑን ለመግለጽ ነዉ። ለወጣዉ የቆጠራ አዋጅ ተፈጻሚነትና ለቆጠራዉ መሳካት ከማዕከል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ የቆጠራ ኮሚሽን የሚቋቋም መሆኑን እንደዚሁም በተዋረድ የእነዚህ ኮሚሽኖች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት፣ በመረጃ መስጠት የመተባበር ግዴታ፣ የመረጃዎች ምስጥራዊነት፣ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ በማይሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ ሊወሰድ የሚችለዉን ቅጣት እንዲይዝ ተደርጓል።

### 4.1.3. የቆጠራ ካርታ ማዘጋጀት፣

ከቆጠራው የዝግጅት ሥራዎች አንዱና ዋነኛው የቆጠራ ካርታ ሥራ በመሆኑ የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ይህን ሥራ የሚከታተልና የሚያስፈጽም የቆጠራ ካርታ ዝግጅት የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም አድርጓል። በተቋቋመው ኮሚቴ አማካኝነትና አስተባባሪነትም የሚከተሉት ሥራዎች ተከናውነዋል።

#### ሀ. የቆጠራ ካርታ ሥራ መመሪያና ልዩ ልዩ ቅጾች ማዘጋጀትና ማሳተም:

በቆጠራዉ ወቅት አንድም ሰው ወይም ቤት ሳይቆጠር እንዳይቀር እንዲሁም ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይቆጠር ለማድረግ የቆጠራው ተግባር ከመከናወኑ በፊት የቆጠራ ቦታና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ቆጠራዉን ለማስፈጸም የቆጠራ ቦታ ካርታ ማዘጋጀት በቆጠራው የሚሰማራውን የሰው ኃይል /የቆጣሪዎችንና የተቆጣጠሪዎችን/ ብዛት ለመገመት፣ የሎጂስቲክስ ፍላጎት ለመተመን፣ የሥራ ጥራትን ለመቆጣጠር ከማስቻሉም በላይ ወደፊት ለሚካሄዱ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የዲሞግራፊያዊ ጥናቶች ለናሙና መረጣ መሠረት በመሆንም ያገለግላል። በመሆኑም ስለቆጠራው ካርታ አሠራር የሚገልጽ/የሚያስረዳ ዝርዝር መመሪያ በማዘጋጀት ይኸው በመስክ ሥራ ወቅት ተግባራዊ ተደርጓል። የተሠሩትን ካርታዎች በሥርዓት ለማስቀመጥና ለመቆጣጠር ለሥራ በሚፈለጉበት ወቅት ደግሞ ለጠያቂዉ ክፍል ለማስረከብ የሚያገለግሉ ቅጾች ተዘጋጅተውና በበቂ ቅጂ ታትመው ሥራ ላይ ውለዋል።

#### ለ. ለቆጠራ ካርታ ሥራ የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች ግዢና ሥርጭት

የካርታ የመስክ ሥራ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ በርካታ አላቂና ቋሚ ዕቃዎች በመግዛትና በማሰባሰብ በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። እነዚህም የካምፕ ዕቃዎች /ድንኳን፣ የመኝታ ከረጢት፣ የሸራ አልጋ፣ የማብሰያ ዕቃዎች...ወዘተ/፣ የጽሕፈት መሣሪያዎች ግዢ እንደዚሁም ከካርታ ሥራ ባለሥልጣንና ከሌሎች መሥሪያ ቤቶች የተሰበሰቡ መሠረተ ካርታዎች /Base Maps/ ናቸው።

## ሐ. በቆጠራ ካርታ ሥራ ለሚሳተፉ ሠራተኞች ሥልጠና መስጠትና ማሠማራት

የቆጠራ ካርታ ሥራውን ለማስጀመር በሁለት ደረጃ የተዘጋጀ ሥልጠና ተሰጥቷል። ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ዋናው መሥሪያ ቤት 180 ሠራተኞች የተሳተፉበት የአሠልጣኞች ሥልጠና እንደዚሁም በሁለተኛ ደረጃ በባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች 1002 የካርታ ሠራተኞችና ተቆጣጣሪዎችን ለሁለት ወራት እንዲሠለጥኑ በማድረግና በ88 ቡድኖች በማደራጀት በመላ ሀገሪቱ በጥቅምት ወር 1985 ዓ.ም ሥራው እንዲጀመር ተደርጓል።

በሌላ በኩል የቆጠራዉን ካርታ ሥራ ለማጠናቀቅ የታቀደው ከ12-15 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ስለነበር በተሽከርካሪ መኪናዎችና በሌሎች የሎጅስቲክስ ዕቃዎች አለመሟላት ምክንያት 150 ቡድኖች አሟልቶ ለማሠማራት አልተቻለም ነበር። ስለሆነም ይህንኑ ችግር ለመንገሥት በማሳወቅ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት አማካኝነት 66 ተጨማሪ የመስክ መኪናዎች በመመደባቸው ተጨማሪ የቆጠራ ካርታ ሠራተኞች በመመልመልና በማሠልጠን በቆጠራዉ ካርታ ሥራ የተሠማራዉን የቡድኖች ብዛት ወደ 150 ከፍ በማድረግ ሥራውን በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ተችሏል።

## መ. በመስክ የካርታ ሥራ ክንውን

የቆጠራ ካርታ አዘገጃጀት በወጣለት ዝርዝር መመሪያ መሠረት የተፈጸመ ሲሆን ክንውኑም ባለ 1:50,000 መስፈርት ካርታንና የከተሞች ማስተር ፕላኖችን እንደ መሠረታዊ ካርታ (Base maps) በመጠቀም በገጠር በእያንዳንዱ ወረዳ ዉስጥ የሚገኙ የገበሬ ማህበራት ወሰንን በመከለል የቤቶችና የቤተሰብ ኃላፊዎች ምዝገባ ተካሂዷል። ከዚያም በአማካይ ከ150-200 ቤተሰቦችን የያዘ ቦታ እንደ አንድ የቆጠራ ቦታ ሲከለል ከ5-6 አጠገብ ለአጠገብ የሚገኙ የቆጠራ ቦታዎቸ ደግሞ እንደ አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ በመሆን ተከልሏል። በከተማም የቀበሌ ወሰኖችን በማስተር ፕላን ካርታዎች ላይ በማስፈር የቤቶችና የቤተሰብ ኃላፊዎች ምዝገባ ከተካሄደ በኋላ በአማካይ ከ150-200 ቤቶችን የያዘ ቦታ እንደ አንድ የቆጠራ ቦታ ሲከለል ከ5-6 አጠገብ ለአጠገብ የሚገኙ የቆጠራ ቦታዎች

ደግሞ እንደ አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ ሆነዉ ተከልሏል። የማስተር ፕላን ካርታ የሌላቸው ትንንሽ ከተሞችም የካርታ ንድፍ (Sketch map) በማዘጋጀት የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ ዝግጅት በተመሳሳይ ሁኔታ ተካሂዷል።

በዚህ መልኩ የተዘጋጁት የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች ለእያንዳንዱ ቆጣሪና ተቆጣጣሪ በግዳል ካርታዎቹ በያዙት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምልክቶችና መገለጫዎች በመታገዝ የተመደቡበትን የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታ አውቀው የቆጠራውን ሥራ አከናዉነዋል። በዚህ መሠረት 11,420 የመቆጣጠሪያና 58,702 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ተዘጋጅተው ለታለሙት ዓላማ ዉለዋል። ከዚህም በተጨማሪ አሁንም በመካሄድና ወደፊት ለሚካሄዱ የናሙና ጥናቶች እንደፍሬም ሆነው ያገለግላሉ። በዚህ አጋጣሚ በተሰበሰቡ ዝርዝር ካርታ ነክ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ የአስተዳደር ክፍፍልን የሚያሣዩ ካርታዎች ማለትም የኢትዮጵያ ካርታ በክልል፥ በዞንና በወረዳ፥ የብሄራዊ ክልሎች ካርታ በዞንና በወረዳ እንደዚሁም የወረዳዎች ካርታ በገበሬ ማህበራትና በቆጠራ ቦታዎች ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምልክቶች ጋር ከፋፍሎ የሚያሳዩ ካርታዎች ለማዘጋጀት ተችሏል። የእነዚህ ካርታዎች ተፈላጊነትና ጠቃሚነት የተለያዩ ተጠቃሚዎች ከሚያቀርቡት ጥያቄ ብዛት ከፍተኛ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

### 4.1.4. የዉጪ እርዳታ ለማግኘት ፕሮጀክት ዶክመንት ዝግጅት፥

ለቆጠራዉ ተግባር ማስፈፀሚያ ከመንግሥት ከሚመደበዉ በጀት በተጨማሪ ከዉጪ እርዳታ በማስፈለጉ ስለቆጠራዉ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የስምምነት ዶኩመንት ተዘጋጅቶ ነበር። ይህንንም ፕሮጀክት ዶኩመንት ለእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በማሰራጨት በወቅቱ በነበረዉ በዉጪ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አማካይነት የእርዳታ ለጋሽ ድርጅቶችና አገሮች የተሳተፉበት ስብሰባ በመጥራት አወያይቶ ለቆጠራዉ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚሰጡትን እርዳታ በተመለከተ ቃል እንዲገቡ ተደርጓል። በዚህም መሠረት ለቆጠራዉ ማስፈጸሚያ የሚረዳ የኤክስፐርቶች የቴክኒክ ድጋፍና በተለይም መጠኑ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብና የማቴሪያል እርዳታ ለማግኘት ተችሏል።

### 4.1.5. <u>የቆጠራ መጠይቆች፣ መመሪያዎችና ቅጾች ዝግጅት፣</u>

ቆጠራውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች መጠይቆችና ልዩ ልዩ ቅጾች በመ/ቤቱ ውስጥ በተቋቋመ ቴክኒክ ኮሚቴ አማካይነት ተዘጋጅቶ የመረጃው ተጠቃሚ ለሆኑ መሥሪያ ቤቶችና በአገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ቆጠራው ለሚመለከታቸው የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስለመጠይቁ ይዘትና አቀራረጽ ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ተሠራጭቶ የአንድ ቀን ሴሚናርም ተካሂዷል። በተገኙትም አስተያየቶች መሠረት በመመሪያዎችና በመጠይቆቹ ላይ አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎባቸው ለሙከራ ቆጠራው ጥናት እንዲውሉ ተደርጓል።

### 4.1.6. <u>የሙከራ ቆጠራ ጥናት ማካሄድ</u>

የሕዝብና ቤት ቆጠራን ለማካሄድ የተግባር እንቅስቃሴ ውስጥ ከመግባቱ በፊት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በቅድሚያ አውቆ የመፍትሄ እርምጃዎችና የተለየ የሥራ ስልት ለመቀየስ የሙከራ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል። የዚህ ጥናት መካሄድ ዓላማ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- ለቆጠራው ሥራ የተዘጋጁት መጠይቆች፣ መመሪያዎችና የቆጠራ ካርታዎች ብቃት ትክክለኛነት ለመፈተሽ፣

- ለሥልጠናና በቆጠራው ወቅት ከአንድ ቤተሰብ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስፈልገው አማካይ ጊዜ ለማወቅ፣

- ለመስክ ሠራተኞች መጓጓዣ፣ ምግብ፣ መጠለያ ...ወዘተ በማግኘት ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማወቅ፣

- የአስተዳደር መዋቅሮች ለቆጠራው ሥራ የሚሰጡትን ድጋፍ በተመለከተ ፍንጭ ለማግኘትና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል፣

የሙከራ ቆጠራዉ በአገሪቱ በሙላ በናሙና በተመረጡ አካባቢዎች ተካሂዷል። የናሙና አመራረጡም የተለያዩ ማህበራዊ፣ ዲሞግራፊያዊና መልከአምድራዊ ሁኔታዎችን ሊያንፀባርቁ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የተከናወነ ነዉ። በዚህ መሠረት በሙላ አገሪቱ 30 የመቆጣጠሪያ ቦታዎችና 150 የቆጠራ ቦታዎች ተመርጠዋል። ከእነዚህ መሀከል 19 የመቆጣጠሪያ ቦታዎች የገጠር ሲሆኑ የተቀሩት 11 ደግሞ የከተማ ናቸዉ። በዚሁ የሙከራ ጥናት ወደ 30,000 ቤተሰቦችን ለመሸፈን ተችሏል። የጥናቱ ዉጤትም የእርምት እርምጃ ሊደረጉ የሚገባቸዉ ጉዳዮችን በማመልከት በዋናዉ ቆጠራ ጊዜ ችግሮችን ለማስወገድ ረድቷል።

4.1.7. <u>የቆጠራ መጠይቆች፣ ቅጾችና መመሪያዎች ዝግጅት ፣ ሕትመትና ስርጭት፣</u>

በሙከራ ቆጠራው በተገኘው ልምድ የዳበሩና ማሻሻያ የተደረገባቸው 14.1 ሚሊዮን ቅጅ አጭርና ረዥም መጠይቆች፣ ለዶክሜንቶች ርክብክብ ለሌላም ሥራ የሚያገለግሉ 632,400 ቅጂ ልዩ ልዩ ቅጾችና በቆጠራው ስለሚሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነትና ትርጓሜ እንደዚሁም ስለአንዳንድ ጽንሰ ሐሳቦች ትክክለኛ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ 98,400 ቅጅ ልዩ ልዩ መመሪያዎች ተዘጋጅተውና ታትመው ተሠርቶባቸዋል።

የአጭርና የረዥም መጠይቆች ምንነትና ይዘት ወደ ኋላ የሚነሳ ሲሆን መመሪያዎችን በሚመለከት ግን የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያዎች መሠረተ ሃሳብ የሚከተለው ነው።

ሀ. <u>የቆጣሪዎች መመሪያን በተመለከተ</u>

ቆጣሪዎች ጥራቱን የጠበቀና አስተማማኝ መረጃ እንዲሰበሰቡ ለማስቻል በቆጠራው ስለሚሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነት፣ በሚሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ ስለሚገኙ አንዳንድ ጽንሰ ሐሳቦች ትርጓሜ፣ መረጃ የሚሰበሰብባቸዉ መጠይቆች፣ የቤቶችና

ቤተሰቦች መመዝገቢያ፣ ...ወዘተ. እንዴት እንደሚሞሉ፣ እንደዚሁም ስለቆጠራ ካርታ አጠቃቀም..ወዘተ በቅድሚያ መረዳት/ማወቅ ይኖርባቸዋል።

በዚሁ መሠረት በቀጥታ በቆጠራው ሥራ ላይ ለተሳተፈው በርካታ የሰው ኃይል ስለመመሪያው ይዘት በማብራራትና በውይይት ደግሞ ይበልጥ ግልጽ በማድረግ ቆጣሪዎች ጥራቱን የጠበቀ መረጃ እንዲሰበስቡ ተደርጓል።

ለ. <u>የተቆጣጣሪዎች መመሪያን በተመለከተ</u>

የተቆጣጣሪዎች ተግባር በቆጠራው ለሚሰበሰቡት መረጃዎች ጥራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። በመሆኑም እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ በተመደበበት የመቆጣጠሪያ ቦታ የተሠማሩትን ቆጣሪዎች በማስተባበር፣ በመቆጣጠር፣ በመከታተልና በመርዳት የቆጠራው ሥራ በመመሪያው መሠረት እንዲከናወን የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ይህንን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት እንዲችልም ተቆጣጣሪው የካርታ አጠቃቀም፣ የምዝገባ፣ የቆጣሪዎች፣ የተቆጣጣሪዎችና ሌሎች መመሪያዎችን ጥምር ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል።

በዚሁ ምክንያት ለተቆጣጣሪዎች ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ለይ በቂ ዕውቀት በማስጨበጥ አስተማማኝ መረጃ በመመሪያው መሠረት እንዲሰበሰብ የቁጥጥሩን ተግባር እንዲያከናውኑ ተደርጓል።

ሐ. <u>ሌሎች መመሪያዎችንና ቅጾችን በተመለከተ</u>

የቆጠራዉን ተግባር ማስፈጸሚያ የሚዉሉ የተለየዩ መመሪያዎችና ቅጾች ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ከቆጣሪዎችና ከተቆጣጣሪዎች መመሪያ በተጨማሪ የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያ፣ የቆጠራ ጽ/ቤት ሠራተኞች መመሪያ፣ የፋይናንስ አፈጻጸም መመሪያ፣ የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ፣ እንደዚሁም ጊዜያዊ የሕዝብና ቤት

ቆጠራ ድርጅታዊ መዋቅር ከነሙሉ ተግባርና ኃላፊነቱ ጋር ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም የሚከተሉት ቅጾችና መጠይቆች ተዘጋጅተዋል። እነዚህም:-

i. የቤቶችና የቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ፣
ii. ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሄድባቸው የቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ፣
iii. በቆጠራ ጊዜ የቆጣሪ ዕለታዊ የሥራ ክንዉን መመዝገቢያ ቅጽ፣
iv. የቆጠራ ቦታ የሕዝብ ብዛት ማጠቃለያ ቅጽ፣
v. የመቆጣጠሪያ ቦታ የሕዝብ ብዛት ማጠቃለያ ቅጽ፣
vi. የተቆጣጣሪ ዕለታዊ የሥራ ክንዉን መመዝገቢያ ቅጽ፣
vii. ተቆጣጣሪዎች ከወረዳ ቆጠራ ጽ/ቤት የቆጠራ ማቴሪያሎች መረካከቢያ ቅጽ፣
viii. ቆጣሪዎች ከተቆጣጣሪዎች የቆጠራ ማቴሪያሎች መረከቢያ ቅጽ፣
ix. ተቆጣጣሪዎች ከቆጣሪዎች የቆጠራ ማቴሪያሎች መረከቢያ ቅጽ፣
x. ተቆጣጣሪ ለወረዳ ቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊ የቆጠራ ዶኩመንቶችና ማቴሪያሎች ማስረከቢያ ቅጽ፣
xi. ከወረዳ ቆጠራ ጽ/ቤት እስከ ብሄራዊ ቆጠራ ጽ/ቤት የቆጠራ ዶኩመንቶችና ማቴሪያሎች መረካከቢያ ቅጽ፣

- የገጠር አጭር መጠይቅ
- የከተማ አጭር መጠይቅ
- የገጠር ረጅም መጠይቅ
- የከተማ ረጅም መጠይቅ

- የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምደባና መለያ ኮድ ዝርዝር እና

- የአካባቢ መለያ (ጆግራፊካል ኮድ) ኮድ ዝርዝር ናቸው።

### 4.1.8. በከብት አርቢ አካባቢዎች ቆጠራዉ የሚካሄድበት ዘዴን ማጥናት፣

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን በከብት አርቢ አካባቢዎች ቆጠራም ሆነ ልዩ ልዩ ጥናቶች ከዚህ በፊት ያላካሄደ በመሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች በእነዚህ አካባቢዎች ያካሄዳቸዉን ጥናቶች ዉጤት የያዙ ዶኩመንቶችን በማሰባሰብ አስፈላጊዉን ጥናት አካሂዷል። በተጨማሪም ወደነዚህ ከብት አርቢ አካባቢዎች የባለሥልጣኑ መ/ቤት የባለሙያዎች ቡድኖች በማሠማራት በአካባቢዉ ከሚንቀሳቀሱ ሌሎች ድርጅቶች ጋር ተወያይቷል። እንዲሁም ቡዱኖቹ በአካባቢዉ ከመዘዋወርና ባለሥልጣኖችን በማነጋገር ቆጠራዉ መቼና እንዴት መካሄድ እንዳለበት የዉሣኔ ሃሳብ አቅርቧል።

### 4.1.9. የቆጠራ ኮሚሽኖችንና ጽ/ቤቶችን ማቋቋም

የቆጠራዉ ተግባር በአንድ ወይም በተወሰኑ ድርጅቶች አማካይነት ብቻ የሚፈፀም ባለመሆኑ ኮሚሽኖች በተዋረድ እንዲቋቋሙ በአዋጅ ሲወሰን የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣንም በተዋረድ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ሆኖ እንዲያገለግል ተወስኖአል። በዚሁ መሠረት በማዕከል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽኖችና ጽ/ቤቶች እንዲቋቋሙ ተደርጓል። እንደዚሁም በገጠርና በከተማ በቀበሌዎች ደረጃም የሕዝብና ቤት ቆጠራ አስተባባሪ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ሲደረግ በአጠቃላይ ቆጠራዉን ለማስፈፀም የሚያስፈልገዉ ድርጅታዊ መዋቅር ከዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ጋር ተዘጋጅቶ በተግባር ላይ እንዲዉል ተደርጓል። ድርጅታዊ መዋቅሩን በእዝል 1 ይመልከቱ።

### 4.1.10. የሰዉ ኃይል ምልመላ፣ ሥልጠናና ስምሪት፣

#### ሀ የሰዉ ኃይል ምልመላ፣

በ1987 ጥቅምት ወር ለተካሄደዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራን ለማስፈጸም ቁጥሩ እጅግ በርካታ የሆነ የሰዉ ኃይል እንዲሰማራ ተደርጓል። ለእያንዳንዱ ክልል፣ ዞንና ወረዳ

የሚያስፈልጉ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ምልመላ የተፈጸመዉ በየክልሉ፣ በየዞኑና በየወረዳዉ ሲሆን በመመዘኛዉ መሠረት ተፈላጊዉን የሰዉ ኃይል ማሟላት ላልቻሉ ደግሞ ከአጎራባች ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ለመመልመል ሁኔታዉ አስገድዷል።

የቆጠራዉን ሥራ ዳር ለማድረስ በጠቅላላዉ 84,900 የሚደርሱ ሠራተኞች እንደሚያስፈልጉ በታቀደዉ መሠረት 13,650 ተቆጣጣሪዎች፣ 68,250 ቆጣሪዎች፣ እና 3,000 በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተሳትፈዋል።

## ለ     የሰዉ ኃይል ሥልጠና፣

- በቆጠራዉ ለተሰማራዉ የሰዉ ኃይል በሦስት ደረጃ የተያዘ ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን ይኸዉም፣

- በመጀመሪያ ደረጃ በአሠልጣኞች ሥልጠና ለተሳትፎ ወደ 200 ለሚደርሱ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ባልደረቦች በዋናዉ መ/ቤት የ10 ቀናት ሥልጠና ከሐምሌ 13 ቀን 1986 ጀምሮ ተሰጥቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ በባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ቁጥራቸዉ ወደ 1200 ለሚደርሱ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ስለቆጠራዉ የ10 ቀናት ሥልጠና ከነሐሴ 2 ቀን 1986 ጀምሮ ተሰጥቷል።

- በሁለተኛ ደረጃ ቀደም ብሎ ከሠለጠኑት ጋር በመሆን በአሠልጣኝነት ለተሰማሩ ለ2,000 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራንና ከሌሎች መሥሪያ ቤቶች ለተመለመሉ ሠራተኞች በተመረጡ በ32 የማሠልጠኛ ማዕከሎች ስለቆጠራዉ የ10 ቀናት ሥልጠና ከመስከረም 2 ቀን 1987 ጀምሮ ተሰጥቷል።

- በሶስተኛ ደረጃ ዋናዉን ቆጠራ ለሚያካሂዱ 68,250 ቆጣሪዎችና 13,650 ተቆጣጣሪዎች ስለቆጠራዉ የ10 ቀናት ሥልጠና በተመረጡ በ132 የሥልጠና ማዕከሎች ከመስከረም 14 ቀን 1987 ጀምሮ ተሰጥቷል።

ሐ <u>የሰዉ ኃይል ስምሪት፣</u>

- ቆጣሪዎችንና ተቆጣጣሪዎችን ከማሰልጠኛ ማዕከሎች ወደ ወረዳዎች፣ ከወረዳዎች ወደ ምድብ ቦታቸዉ ለማጓጓዝ ተሽከርካሪዎችና፣ የጋማ ከብቶች ጥቅም ላይ ዉለዋል። ይሁን እንጂ በተሽከርካሪም ሆነ በጋማ ከብት መድረስ የማይቻልባቸዉን ቦታዎች ግን በእግር እስከ አምስት ቀን ድረስ በመጓዝ ጭምር ቆጠራዉን ለማካሄድ ተችሏል።

## 4.1.11. ትምህርትና ቅስቀሳ፣

በሕዝብና ቤት ቆጠራ የተሟላ መረጃ ለማግኘት ቆጠራዉ በታቀደዉ ጊዜ ዉስጥ ለማጠናቀቅ ከህብረተሰቡ ቀና ትብብር ማግኘት ወሳኝነት ነበረዉ። ለዚህ ግብ ተፈጻሚነት ህብረተሰቡ የቆጠራዉን ዓላማ በዉል ለመገንዘብ እገዛ የሚያደርግ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ በሬድዮ፣ በቴሌቪዥንና በፕሬስ አማካኝነት የተከናወነ ሲሆን ዝርዝር ሥራዎችም የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- በሬድዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጦች ቃለ መጠይቆችና ማብራሪያዎች ተላልፈዋል።

- አጫጭር ሕዝብና ቤት ቆጠራ ነክ ድራማዎችና መሪ መዝሙር ለሕዝብ እይታና ሰሚ በቴሌቪዥንና በሬድዮ ቀርቧል።

- የተዘጋጁ አጫጭር ጽሁፎችና ካርቶኖች ለሕዝብ ንባብ፣ እይታና ሰሚ በጋዜጦች፣ በቴሌቪዥንና በሬድዮ አማካኝነት ቀርበዋል።

- በተለያዩ መሰብሰቢያ ቦታዎች በሚታዩ ሁኔታ የሚለጠፉ /የሚንጠለጠሉ መፈክሮችና ፖስተሮች/ ተዘጋጅተዉ ተግባሩ ተፈጽሟል።

## 4.2. ዋናዉን ቆጠራ ማካሄድ፡

በዋናው ቆጠራ ወቅት ቆጣሪዎች በተመደቡት የቆጠራ ቦታ ከቤት ቤት በመሄድ በተዘጋጁት መጠይቆች መሠረት ተፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

በተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሕዝብን በሚመለከት በገጠርና በከተማ የተሰበሰበው መረጃ ዓይነት በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው ። የቤት መረጃን አስመልክቶ ግን በገጠርና በከተማ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለማንፀባረቅ ሲባል ተጨማሪ ጥያቄዎች በከተማ ቆጠራ እንዲካተቱ ተደርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በተደረገው ቆጠራ አጭር መጠይቅ የተወሰኑ መረጃዎች ለሁሉም ቤተሰቦች ከቤት ቤት በመዘዋወር የተሰበሰቡ ሲሆን ዝርዝር መረጃዎቸ ደግሞ ረዥም መጠይቅ በመጠቀም በናሙና ለተመረጡ ቤተሰቦች ብቻ ከቤት ቤት በመሄድ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚህ የቆጠራ ሂደት ለእያንዳንዱ ቆጠራ ቦታ አንድ አንድ ቆጣሪ የተመደበ ሲሆን ቆጣሪዉ ከቤት ቤት በመሄድ ለቆጠራዉ የተዘጋጁትን መጠይቆች በመሙላት ቆጠራዉን አካሂዷል። ጥራቱንም ለመቆጣጠር ከ5-6 ቆጣሪዎች አንድ ተቆጣጣሪ ተመድቦላቸዉ ነበር።

በዚሁ መሠረት በዋናዉ ቆጠራ ወቅት የተሰበሰቡት መረጃዎች የሚከተሉት ሲሆኑ የገጠርና የከተማ ረዥም መጠይቅ እንደዚሁም የገጠርና የከተማ አጭር መጠይቅ በአዝል 2 ቀርቧል።

### 4.2.1 ለሁሉም ቤተሰቦች አጭር መጠይቅ በመጠቀም የተሰበሰቡ መረጃዎች

i. የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም
ii. የነዋሪ ሁኔታ
iii. ፆታ
iv. ዕድሜ
v. ሃይማኖት
vi. የአፍ መፍቻ ቋንቋ
vii. ተጨማሪ ቋንቋ የመናገር ችሎታ
viii. ብሄረሰብ
ix. የጋብቻ ሁኔታ

### 4.2.2 በናሙና ለተመረጡ ቤተሰቦች ረዥም መጠይቅ በመጠቀም የተሰበሰቡ መረጃዎች

ከላይ በተራ ቁ. 4.2.1. ከተዘረዘሩት በተጨማሪ በረዥሙ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚከተሉት መረጃዎች ተሰብስበዋል:-

i. እዚህ ወረዳ ገጠር ውስጥ ያለማቋረጥ ስንት ዓመት ኖረዋል?
ii. እዚህ ከተማ ዉስጥ ያለማቋርጥ ስንት ዓመት ኖረዋል?
iii. ቀድሞ ይኖሩበት የነበረው ስፍራ ከተማ ከነበር የከተማው ስም ይጻፍ፣ገጠር ከነበር "ገጠር" ይጻፍ
iv. የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታ
v. በትምህርት ቤት የመማር ሁኔታ
vi. የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል/የማንበብና የመጻፍ ችሎታ/
vii. በምርታማ ሥራ መሳተፍ
viii. ሥራ ካልሠሩ ያልሠሩበት ምክንያት
ix. የሥራ ዓይነት

x. የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት

xi. የቅጥር ሁኔታ

xii. ጠቅላላ በሕይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት

xiii. ባለፉት 12 ወራት በሕይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት

### 4.2.3 <u>በገጠር ስለቤቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች</u>

በገጠር ስለቤቶቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች በገጠር የሕዝብና ቤት ቆጠራ ረኾም መጠይቅ አማካኝነት ሲሆን መረጃዎቹም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል:-

i. የቤቱ አገልግሎት

ii. የቤቱ አይነት

iii. የቤቱ ግድግዳ በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ

iv. የቤቱ ጣሪያ በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ

v. የቤቱ ክፍሎች ብዛት

vi. ቤተሰቡ በሚያድርበት ቤት ከብቶች ያድሩ እንደሆነ

vii. የቤቱ የማድቤት ሁኔታ

viii. ቤቱ ለምግብ ማብሰያ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው የማገዶ ዓይነት

ix. ቤቱ ያለው የመጸዳጃ አገልግሎት ዓይነት

x. የቤቱ ነዋሪዎች የመጠጥ ውሃ ከየት እንደሚያገኙ

xi. በቤቱ ሬዲዮ መኖር

### 4.2.4 <u>በከተማ ስለቤቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች</u>

በከተማ ስለቤቶቹ የተሰበሰቡት መረጃዎች በከተማ ረኾም የሕዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቅ አማካኝነት ሲሆን መረጃዎቹም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል:-

i. የቤቱ አገልግሎት

ii. የቤቱ ዓይነት

iii. በቤቱ ስንት መደበኛ ቤተሰቦች እንደሚኖሩ

iv. በቤቱ ስንት መደበኛ የቤተሰብ (ቤተሰቦች) አባሎች እንደሚኖሩ

v. ቤቱ የሚገኝበት የሕንፃ ዓይነት

vi. ቤቱ ከተሠራ ስንት ዓመት እንደሆነው

vii. የቤቱ ግድግዳ በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ

viii. የቤቱ ጣሪያ በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ

ix. የቤቱ ኮርኒስ በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ

x. የቤቱ ወለል በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ

xi. ቤቱ ስንት ክፍሎች እንዳሉት

xii. የቤቱ ይዞት

xiii. ቤቱ የሚከራይ ከሆነ በወር የሚከፈለው የኪራይ መጠን

xiv. ቤቱ ያለው የማድቤት ዓይነት

xv. የቤቱ ነዋሪዎች ለምግብ ማብሰያ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት ማገዶ ዓይነት

xvi. የቤቱ ነዋሪዎች የመጠጥ ውሃ በአብዛኛው ከየት እንደሚያገኙ

xvii. ቤቱ ያለው የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ዓይነት

xviii. ቤቱ ያለው የመጸዳጃ አገልግሎት ዓይነት

xix. ቤቱ ያለው የመብራት ዓይነት

xx. በቤቱ ሬዲዮ መኖር

xxi. በቤቱ ቴሌፎን መኖር

xxii. በቤቱ ቴሌቪዥን መኖር ያካትቱ ናቸዉ።

## 4.3. የድህረ ቆጠራ ሥራዎች፣

ይህ ተግባር የሚከተሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል። እነዚህም፣

- በቆጠራው መረጃ የተሰበሰበባቸው ዶኩመንቶችን ወደ ዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ፣
- የድህረ ቆጠራ ጥናት ማካሄድ፣
- የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ማከናወን፣
- በቆጠራው የተሰባሰቡ መረጃዎችን በኮምፒውተር ውስጥ ማስገባት፣
- መረጃዉን በኮምፒዩተር አቀነባብሮ የቆጠራዉን ዉጤት የሚሳዩ ሠንጠረዦች (tabulation) ማዉጣት፣
- ከቆጠራው የተገኘውን መረጃ መገምገም፣ መተንተንና ሪፖርት ማዘጋጀት፣ እና
- የቆጠራውን ውጤት የሚያሳይ ሪፖርት በማሳተም ለመረጃ ተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣ ናቸው።

### 4.3.1 በቆጠራዉ መረጃ የተሰበሰበባቸዉ ዶኩመንቶችን ወደ ዋናዉ መ/ቤት ማሰባሰብ

በቆጠራዉ ወቅት መረጃ እንዲሰበሰቡባቸዉ በተዋረድ የተሠራጩት ዶኩመንቶች ማለትም መመሪያዎች፣ መጠይቆች፣ ቅጾች፣ ከዋናዉ ቆጠራ ፍጻሜ በኋላ ማለትም

መረጃዉ ተሰብስቦ ካበቃ በኋላ ወደ ዋናዉ ጽ/ቤት መመለስ አለባቸዉ። በመሆኑም እነዚህ ዶኩመንቶች በተሠራጩበት ሁኔታ ተሰባስበዉ ወደ ዋናዉ መ/ቤት ተልከዉ ለአያያዝና ለጥበቃ በሚያመች መልኩ ተደራጅተዉ እንዲቀመጡ ተደርጓል።

### 4.3.2 የድህረ ቆጠራ ጥናት

የድህረ ቆጠራ ጥናት የሚከተሉት ዓላማዎችን መሠረት በማድረግ የሚካሄድ የናሙና ጥናት ነዉ።

- የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሽፋንና የመረጃ ጥራት ደረጃን መገምገም፣
- ወደፊት ለሚካሄዱ ተመሳሳይ የቆጠራ ሥራዎች የሚጠቅሙ የፅንሰ-ሃሳቦችና የቅደም ተከተሎች ማሻሻያ ሐሳቦችን ማግኘት፣
- ለቆጠራዉ ሥራ የተዘጋጁት የቆጠራ ቦታ ካርታዎችን የጥራት ደረጃ ወደፊት ለሚካሄዱ ጥናቶች የመነሻነት ብቃት መገምገም፣

በየትኛዉም ሀገር ቢሆን ፍጹም የሆነ ቆጠራ እንደማይኖር የሚታወቅ ጉዳይ ቢሆንም በተለይም ደግሞ በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገሮች የሚካሄዱ ቆጠራዎች የሽፋን (coverage) ደረጃና የመረጃ ጥራት (content) ለበለጠ አንጻራዊ ስህተት የተጋለጡ ናቸዉ። በሕዝብና ቤት ቆጠራዎች የሽፋን ስህተቶች (coverage errors) በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ሲሆኑ ከነዚህ ምክንያቶች መካከል በቆጠራዉ የመስክ ሥራ ወቅት ቆጣሪዎች የተመደቡባቸዉን የቆጠራ ቦታዎች ድንበር ሙሉ በሙሉ ያለ ስህተት ለመለየት መቸገር፣ ቤተሰቦችን እና ግለሰቦችን ከአንድ ጊዜ በላይ መቁጠር ወይም ጨርሶ ያለመቁጠር ዋነኞቹ ናቸዉ። በሌላ በኩል ደግሞ በቆጠራዉ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የጥራት ግድፈት ቀዳሚ መንስዔ መረጃ ሰጪዎች ለሚቀርቡላቸዉ ጥያቄዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ትክክለኛ መልስ ያለመስጠት ነዉ።

የነዚህን ችግሮች የመከሰት ዕድል በመገንዘብ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የቆጠራን የሽፋንና የመረጃ ጥራት ደረጃን ለመገምገም ከሚያስችሉት ዘዴዎች አንዱ የሆነዉን የድህረ ቆጠራ ጥናትን የ1987 ሕዝብና ቤት ቆጠራ የመስክ ሥራ በተጠናቀቀ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ለማካሄድ ወሰነ።

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ ከአፋርና ከሶማሌ ብሄራዊ ክልሎች በስተቀር በሌሎች ብሄራዊ ክልሎች በናሙና በተመረጡ 285 የቆጠራ ቦታዎች የድህረ ቆጠራ ጥናቱ ተካሂዷል።

በ1987 የተካሄደዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሁለተኛዉ ሀገር አቀፍ ቆጠራ ሲሆን በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ልምድ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲወዳደር በጣም አነስተኛ እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህም በመነሳት ከሌሎች ሀገሮች የቆጠራ ዉጤት ደረጃ አንጻር ሲታይ የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሽፋን ደረጃና የመረጃ ጥራት አጥጋቢ እንደሆነ የጥናቱ ዉጤት ያመለክታል። ከተካሄደዉ የድህረ ቆጠራ ጥናት ግኝት በመነሳትም የወደፊት ተመሳሳይ ክንዉኖችን የጥራትና የብቃት ደረጃ ለማጎልበት የሚረዳ ጠንካራ መሠረትም ለመጣል እንደተቻለ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ያምናል።

4.3.3 <u>የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራን ማከናወን</u>

የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃን የያዙ መጠይቆች ወደ ዋናዉ መ/ቤት ከደረሰ በኋላ መረጃዉን የያዙት መጠይቆች በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በገጠር፣ በገበሬ ማሕበር፣ እና በከተማ በቀበሌ እንዲሁም በቆጠራ ቦታዎች እንዲደራጁ ተደርጓል። ከዚያም በመቀጠል መረጃዎቹ ኮምፒዩተር ዉስጥ ለማስገባት አመቺ እንዲሆኑ መረጃዎቹን ኮድ በማድረግና የመረጃዉንም ጥራት ለመጠበቅ ኢዲትና ቬሪፋይ በማድረግ ወደ ዳታ ኢንትሪ ክፍል ተልከዋል። በዳታ ኢንትሪ ጊዜ ለሚነሱ ጥያቄዎች 12 ኢዲተሮች ተመድበዉ ለሥራዉ ጥራትና ቅልጥፍና አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ኤዲቲንግ:- ማለት በተሰጠዉ መመሪያ መሠረት የተለያዩ እምዶችን ካመግከሩ በኋላ በተሰበሰበዉ መረጃ ላይ አስፈላጊዉን እርማት ማድረግ ነዉ።

ኮዲንግ:- ማለት መጠይቁ ላይ በቃላት የተሰጡትን መልሶች ወደ አኃዝ መለወጥ ነዉ። ይህን አኃዝ በቀላሉ ወደ ኮምፒዩተር ለማስተላለፍ ስለሚቻል መረጃዉን ለማተንባበር ይረዳል። ለዚህም የሚያገለግል ኮድ ቡክ በቅድሚያ ተዘጋጅቶ ነበር።

ቬሪፊኬሽን:- ማለት ኤዲተሩ በተሰጠዉ መመሪያና ስልጠና መሠረት በትክክል ኤዲት ማድረጉንና ተገቢዉ ኮድ መጻፉን በመመርመር ማረጋገጥ ሲሆን በትክክል በመመሪያዉ መሠረት የማይሠራን ሠራተኛ በመምከር ተዉግሬ መመሪያ በመስጠት ጥራት ያለዉ ስራ እንዲሠራ ማድረግ ነዉ።

<u>የኤዲቲንግ ኮዲንግ ሥራ አፈጻጸም</u>

የሁለተኛ ዙር የሕዝብና ቤት ቆጠራ በአንድ የኤዲቲንግ ኃላፊ፣ በሶስት ከፍተኛ ሱፐርቫይዘሮች፣ በ12 ዳታ ኤዲተር ሱፐርቫይዘሮች፣ በ80 ኤዲተርስና ኮደርስ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ተግባር በ12 ወራት ዉስጥ ተከናዉና ተጠናቋል።

ይህም በ1987 ዓ.ም. ከታህሣሥ 1 ቀን 1987 እስከ ሰኔ 30/1987 ዓ.ም. 34,169 የቆጠራ ቦታዎች እና ከሐምሌ 1 ቀን 1987 እስከ ጥር 30 ቀን 1988 ዓ.ም. 29,310 የቆጠራ ቦታዎች በድምሩ 63,479 የቆጠራ ቦታዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ኤዲት፣ ኮድና ቬሪፋይድ ሆነዋል።

4.3.4. <u>በቆጠራዉ የተሰበሰቡ መረጃዎች በኮምፒዩተር ዉስጥ ማስገባት (ዳታ ኢንትሪ)</u>

ዳታ ኢንትሪ:- ማለት የተሰበሰቡ መረጃዎችን ኤዲትና ኮድ ከተደረጉ በኋላ በኮምፒዩተር ላይ መቅረጽ ማለት ነዉ።

በጥቅምት 1987 ዓ.ም. የተካሄደዉን የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዉን በኮምፒዩተር ለማስገባት 180 የኮንትራት ሠራተኞች ተቀጥረዉ አስፈላጊዉ ሥልጠና ተሰጥቶአቸዉ ከጥር 1 ቀን 1987 ጀምሮ እስከ የካቲት 30 ቀን 1988 ዓ.ም. ባሉት 14 ወራት ይህ ተግባር ተጠናቋል።

ይህንን ተግባር ለማከናወን 100 የፐርሶናል ኮምፒዩተሮች በሥራ ላይ ዉለዋል። ለዚሁ ተግባር የተመደቡት 180 የዳታ ኢንትሪ ሠራተኞች በሁለት ፈረቃ ሥራቸዉን ያከናዉኑ ነበር። የመጀመሪያዉ ፈረቃ ከጥዋቱ 1 ሰዓት እስከ ቀኑ 7 ሰዓት የሁለተኛዉ ፈረቃ ከቀኑ 7 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ተኩል ድረስ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ይህንን ተግባር ሲያከናዉን ነበር። ከዚህም በተጨማሪ አንድ ዳታ ኢንትሪ ኃላፊ፣ ሁለት የፈረቃ ሱፐርቫይዘሮች፣ ለአራት ክፍል በሁለት ፈረቃ የተመደቡ ሁለት ሁለት ሱፐርቫይዘሮች በጠቅላላዉ አሥራ ስድስት የክፍል ሱፐርቫይዘሮች ተካፋይ ሆነዋል።

በዚህም ሁናቴ መረጃዉን በኮምፒዩተር የመቅረጽ ተግባር ለ28,595 ቆጠራ ቦታዎች ከጥር 1 ቀን 1987 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1987 ድረስ ባሉት ስድስት ወራት ተጠናቋል። በዚሁ መሠረት ሥራዉን በመቀጠል ይህ ተግባር ለ34,884 ቆጠራ ቦታዎችም ደግሞ ከሐምሌ 1ቀን 1987 ጀምሮ እስከ የካቲት 30ቀን 1988 ድረስ ባሉት ስምንት ወራት ተጠናቋል።

### 4.3.5 መረጃዉ በኮምፒዩተር አቀነባበር የቆጠራዉን ዉጤት የሚያሳዩ ሠንጠረዦች (Tabulation) ማዉጣት

አራት ፐሮግራመሮች በ6 ኮምፒዩተሮች በመጠቀም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሥራዎች ተከናዉነዋል።

- ኮምፒዩተር ኤዲቲንግ (ኮምፒዩተር መረጃ እርማት)
- ማባዣ ቁጥሮችን ማዘጋጀትና መጠቀም

በዚሁ መሠረት የቆጠራዉን ዉጤት የሚያሳዩ:-

5,072 የሥነ ሕዝብ ትንተና ልዩ ልዩ (ሰንጠረዦች)

2,397 የቤት መረጃ ትንተና ልዩ ልዩ (ሰንጠረዦች) ወጥተዉ ለሕትመት ተዘጋጅተዋል።

## 5. የሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ስርጭት፣

የመረጃ ቅንብር ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ተከታዩ ሥራ የሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት ሥራ ነዉ። የሪፖርት ዝግጅቱ ሥራ በሁለት ክፍሎች ማለት በመጀመሪያ ደረጃ Statistical Report በሁለተኛ ደረጃ Analytical Report ለማዉጣት በታቀደዉ መሠረት:-

- የአሥሩ ብሄራዊ ክልሎች Statistical Report ማለትም የአማራ 5ጥራዞች፣ የኦሮሚያ 6ጥራዞች፣ የደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰብና ሕዝቦች 5ጥራዞች፣ የትግራይ፣ የጋምቤላ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ፣ የሐረሪ፣ የአዲስ አበባ፣ የድሬዳዋና የአፋር ለእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ ጥራዞች በአጠቃላይ 23 ጥራዞች ተዘጋጅተዉ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል።

- በተጨማሪም ለያንዳንዱ ክልል የቆጠራዉን ዉጤት በአጭሩ የሚገልጽ ሪፖርት (Summary Report) ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

በቆጠራዉ በተገኘዉ ዉጤት መሠረት የእነዚህ ብሄራዊ ክልሎች የሕዝብ ብዛት በጾታ፣ በከተማና በገጠር ከዚህ በታች በቀረበዉ ሠንጠረዥ ተመልክቷል። በሠንጠረዡም የተመለከተዉ የሕዝብ ብዛት በጥቅምት ወር 1987 የነበረዉ ሁኔታን የሚያንፀባርቅ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የሕዝቡ ብዛት ከዚህ ከፍ እንደሚል ይጠበቃል። ይኸዉም ባለዉ ዓመታዊ የሕዝብ ዕድገት መጠን (Annual Population Growth Rate) ሲሠላ መጠነኛ ጭማሪ እንደሚኖረዉ መታወቅ ይኖርበታል።

## በጥቅምት 1987 በአገር አቀፍ ደረጃ የተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት የብሔራዊ ክልሎች ሕዝብ ብዛት በፆታ እንዲሁም በገጠርና በከተማ

| ተራ ቁጥር | ብሔራዊ ክልል | በፆታ | | | በመኖሪያ ቦታ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ከተማ | ገጠር | ድምር |
| 1 | ትግራይ | 1,542,165 | 1,594,102 | 3,136,267 | 468,478 | 2,667,789 | 3,136,267 |
| 2 | አማራ | 6,947,546 | 6,886,751 | 13,834,297 | 1,265,315 | 12,568,982 | 13,834,297 |
| 3 | ኦሮሚያ | 9,371,228 | 9,361,297 | 18,732,525 | 1,970,088 | 16,762,437 | 18,732,525 |
| 4 | ደቡብ ሕዝቦች | 5,161,787 | 5,215,241 | 10,377,028 | 704,818 | 9,672,210 | 10,377,028 |
| 5 | ቤንሻንጉል ጉምዝ | 233,013 | 227,446 | 460,459 | 36,027 | 424,432 | 460,459 |
| 6 | ጋምቤላ | 92,902 | 88,960 | 181,862 | 27,424 | 154,438 | 181,862 |
| 7 | ሐረሪ | 65,550 | 65,589 | 131,139 | 76,378 | 54,761 | 131,139 |
| 8 | አዲስ አበባ | 1,023,452 | 1,089,285 | 2,112,737 | 2,084,588 | 28,149 | 2,112,737 |
| 9 | ድሬዳዋ አስተዳደር | 127,286 | 124,578 | 251,864 | 173,188 | 78,676 | 251,864 |
| 10 | አፋር | 626,839 | 479,544 | 1,106,383 | 85,879 | 1,020,504 | 1,106,383 |

ከ Statistical Report ዝግጅት በመቀጠልም የAnalytical Report ዝግጅት ሥራ ይካሄዳል። በዚህ ረገድ እስከአሁን:-

- የአዲስ አበባና የትግራይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ Analytical Report ዝግጅት ተጀምሮ በመጠናቀቅ ላይ ነዉ።

- የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዉጤቶችን የፖፕ ማፕ /Pop Map/ ፕሮግራምን በመጠቀም የቆጠራ አትላስ /CENSUS ATLAS/ በኮምፒዩተር የማዘጋጀት ሥራ ተጀምሮአል።

## 5.1 <u>በአፋርና በሶማሌ ብሄራዊ ክልሎች ድጋሚ ቆጠራ ለማካሄድ የተከናወኑ የዝግጅት ተግባራት</u>

እንደሌሎቹ የአገሪቱ ክልሎች ሁሉ በጥቅምት ወር 1987 ዓ.ም የተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በአፋርና በሶማሌ ብሄራዊ ክልሎችም ተካሄዶ ነበር። ይሁን እንጂ ከሁለቱም ብሄራዊ ክልሎች የተሰበሰበው የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ግን በቆጠራው ወቅት በነበረው ሁኔታ ተቀባይነት ባለማግኘቱ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማዕከላዊ ኮሚሽን ድጋሚ ቆጠራ እንዲካሄድ ወስኖአል።

በዚሁ መሠረት ለአፋር ብሄራዊ ክልል ድጋሚ ቆጠራን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ቆጠራ የዝግጅት ተግባሮች ተጠናቀው ከሐምሌ 15-30/1988 ዓ.ም ድረስ ባሉት 15 ቀናት ቆጠራዉ በ4 ዞኖች በተሟላ ሁኔታ ተካሂዶ ተጠናቋል። ሆኖም ቆጠራዉ በአንዱ ዞን ውስጥ ባጋጠመ የትራንስፖርት ችግር ምክንያት እስከ ነሐሴ ወር 1988 መጨረሻ ድረስ ቀጥሎ ለማጠናቀቅ ተችሏል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በሶማሌ ብሄራዊ ክልል ድጋሚ የሕዝና ቤት ቆጠራ በኅዳር ወር 1989 ለማካሄድ ታቅዶ ከዋናው መ/ቤት በክልልና በዞን ደረጃ የቆጠራ ጽ/ቤትና የቴክኒክ ኃላፊ ሆነው እንዲሠሩ የተመደቡ ሠራተኞች ወደ ክልሉ ተልከው ነበር። ነገር

ገን በዚህ ወቅት በክልሉ የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ለማካሄድ የታቀደ ስለነበር ቆጠራዉንና ምርጫዉንም ማካሄድ የክልሉን ባለሥልጣናት ከፍተኛ ተሳትፎና ትብብር የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ነዉ። ስለዚህ ክልሉ ሁለቱን ግዙፍ ተግባራት በአንድነት ለማስተናገድ የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ለመወያየት የክልሉ ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርቶ ምርጫዉ በቅድሚያ እንዲካሄድ ወስኖአል። በዚህም መሠረት ቆጠራዉ መቼና እንዴት እንደሚካሄድ የክልሉ ምክር ቤት ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ጋር በመመካከር የሚወስን መሆኑን በደብዳቤ ገልጿል። በመሆኑም በክልሉና በክልሉ በሚገኙ ዞኖች የቆጠራዉን ዝግጅት ተግባር ለማከናወን የተሰማሩት የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች እንዲመለሱ ተደርጓል።

## 6. በ1989 ዓ.ም የሚከናወኑ ቀጣይ ተግባራት

በሶማሌ ብሄራዊ ክልል ድጋሚ ቆጠራ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ቀሪ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ ቆጠራውን ለማካሄድና በቀጣይነትም የመረጃ ቅንብርና ሪፖርት ዝግጅቱ ተግባራትን ለማከናወን ታቅዷል። ከእነዚህ ተግባራት ጎን ለጎን ለእያንዳንዱ ብሄራዊ ክልልና በብሄራዊ ደረጃ ዝርዝር ያሉ ተንታኝ ሪፖርቶችን (Analytical Reports) የማዘጋጀት ተግባርም እየተካሄደ ነዉ።

## 7. ለቆጠራው ማስፈፀሚያ በሥራ ላይ የዋለ በጀት፣

ሁለተኛዉን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ለማካሄድ ብዛት ያለዉ የሰዉ ኃይል፣ በርካታ ቁሳቁስ፣ የተጠናከረ የሎጅስቲክ ድጋፍ ጠይቋል። በመሆኑም በቆጠራዉ ሥራ ለተሰማሩ ሠራተኞች ደመወዝና የዉሎ አበል ክፍያ እንደዚሁም ለሥራ ማስኬጃ ወጪ የሚሆን ገንዘብ በመንግሥት፣ ተመድቦ የሚከተለዉ መጠን ሥራ ላይ ዉሏል።

## 7.1. በመንግሥት ከተመደበዉ በጀት ዉስጥ ቆጠራዉን በማስፈጸም ተግባራት ላይ የዋለዉ መጠን

- ለካርታ ዝግጅት ሥራ ብር 26,381,459.00
- ለሙከራ ቆጠራ ጥናት ብር 437,711.00
- ለዋናዉ ቆጠራ ሥራ ብር 57,940,897.00
- ለድህረ ቆጠራ ጥናት ብር 507,155.00
- ለመረጃ ቅንብር ሥራ ብር 333,676.00
- ለአፋር ብሄራዊ ክልል ድጋሚ ቆጠራ ብር 4,640,673.00
- ለሶማሌ ብሄራዊ ክልል ድጋሚ ቆጠራ ለቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ወጪ የሆነ ብር 336,364.00
- ድምር ብር 90,577,935.00

## 7.2. ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የተገኘ ድጋፍን በተመለከተ፣

ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ማከናወኛ መንግሥት ከፈቀደዉ በጀት በተጨማሪ ከዓለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ዕርዳታ በማስፈለጉ ስለቆጠራዉ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በማቅረብ በተደረገዉ ጥረት በጥሬ ገንዘብ ብር 3,243,627.42 የገንዘብ ድጋፍ ተገኝቶ በሥራ ላይ ውሏል። ከዚህ ገንዘብ በተጨማሪ በርካታ ልዩ ልዩ ማቴሪያሎች በዕርዳታ የተገኙ ሲሆን እነዚህም 44 ላንድሮቨሮች ከተወሰኑ መለዋወጫዎች ጋር፣ 130 ፐርሰናል ኮሚፒዩተርች ከነመለዋወጫቸው፣ 45,000 የቆጠራ ቦርሳዎች፣ ለሕትመት አገልግሎት የሚዉሉ በርካታ የጽህፈት መሣሪያዎች ናቸዉ። የእነዚህም ማቴሪያሎች ዋጋ በገንዘብ ሲተመን ብር 15,969,376.56 ይሆናል። በመሆኑም ለ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባር በመንግሥትና በዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ተመድቦ /ተሰጥቶ ወጪ የተደረገዉ ገንዘብ ሲጠቃለል ብር 109,790,938.98 ደርሷል።

## 8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፣

የ1987 ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ በተደረገዉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በተለያዩ የአስተዳደር እርከን ያሉ ባለሥልጣናት፣ ሠራተኞች እንዲሁም ሕብረተሰቡ በሰጠዉ ትብብር መሠረት ሥራዉ በአጥጋቢ ሁኔታ ተካሂዷል። ይሁንና በቆጠራዉ ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን፣ በመዘርዘርና የችግሮቹን መንስዔ ከመፍትሄ ሃሳብ ጭምር ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ማዕከላዊ ኮሚሽን እንደዚሁም በተዋረድ ለተቋቋሙት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽኖች በማቅረብ በወቅቱ እንዲወገዱ ጥረት አድርጓል። በወቅቱ አጋጥመዉ ከነበሩት ችግሮች መሃከል:-

ሀ. በዋናዉ መሥሪያ ቤትም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የቆጠራዉን ሥራ በተመቻቸ ሁኔታ ለማካሄድ የሚያስችሉ በቂ ቢሮዎችና ዕቃ ግምጃ ቤቶች አልነበሩም። በመሆኑም የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በዋናዉ መሥሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ተጨማሪ ክፍሎችና መጋዘኖች በማዘጋጀት እንደዚሁም የባለሥልጣኑ

